# ደሕንነት

በሕይወታችን ከምናደርጋቸዉ ታላላቅ ዉሳኔዎች ሁሉ ታላቅ የሆነዉ ዉሳኔ መፅሃፍ ቅዱሳችን ላይ "ለተቀበሉት ሁሉ ግን ÷ በስሙ ለሚ ያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣንን ሰጣቸዉ ። " ( ዮሃንስ ወንጌል ምዕራፍ 1 ÷ 12 ) ስለሆነ ዛሬ ይህንን ዉሳኔ ማድረግ ከወደዱ ÷ ይህን ቅደም ተከተል በመዉሰድ ዉሳኔዎን ሊያፀኑ ይችላሉ ብለን እናምናለን ።

## በእግዚአብሔር ተወደዋል !

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረዉ እንጂ እንዳይጠፋ ፣ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለሙን ( እር ስዎንና እኔን ) እንዲሁ ወዶአል ። " ( ዮሃ 3 ÷ 16 )

ስለዚህ እግዚአብሔር በእርስዎ ላይ ትልቅ አላማ አለዉ !

" ሕይወት እንዲሆንላቸዉ ፣ እንዲበዛላቸዉም መጣሁ ። " ( ዮሃ 10 ÷ 10 )

1. በሃጢያታችን ከእግዚአብሔር ተለይተናል !
   ሁሉ ሃጢያትን ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል ። ( ሮሜ 3 ÷ 23 )

2. የሃጢያት ደሞዛችን የዘላለም ሞት ነዉ !
   " የሃጢያት ደሞዝ ሞት ነዉ ። " ( ሮሜ 6 ÷ 23 )

3. ሃጢያታችን በክርስቶስ ተከፈለልን !
   " ገና ሃጢያተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና ፣
   እግዚአብሔር ለእኛ ያለዉን የራሱን ፍቅር ያስረዳል ። " ( ሮሜ 5 ÷ 8 )

4. ሃጢያታችንን ብንናዘዝ ፣ በክርስቶስ ብንታመንና
   በሕይወታችን ቢነግስ ከሃጢያታችን ነፃ እንሆናለን !
   " የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል ። " ( ሮሜ 10 ÷ 13 )

   ".....ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን
   እንዳነሳዉ በልብህ ብታምን ትድናለህና ፣ ሰዉ በልቡ አምኖ ይፀድቃልና
   በአፉም መስክሮ ይድናልና ። " ( ሮሜ 10 ÷ 9-10 )

ይህንን ቅደም ተከተል ካደረጉ የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነት በልብዎ ከተቀበሉ
" አዲስ ፍጥረት " ነዎት ብለን እናምናለንና ፣ አያሌ አዳዲስ ገጠመኞች በህይወትዎ ይከናወናሉ ።

ለጀመሩት አዲስ መንፈሳዊ ጉዞ እገዛ ይሆንልዎ ዘንድ ይህን እንመክራለን ፦

1. በአካባቢዎ ወዳለ ቤተ-ክርስቲያን እንዲሄዱ !
   " ለፍቅርና ለመልካም ስራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ ፣ በአንዳንዶችም
   ዘንድ ልማድ እንደሆነዉ ÷ መሰብሰባችንን አንተዉ እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ
   ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህንን አድርጉ ። "(ዕብ 10 ÷ 24-25)

2. የዉሃ ጥምቀትን ስርአት ይቀበሉ !
   የክርስቶስ መሆንዎን የሚያሳዩበት መንገድ ነዉና ።
   ኢትዮጵያዊዉ ጃንደረባ እንዳለ ፦

   " እነሆ ዉሃ ! እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድን ነዉ ? " ( የሐዋ 8 ÷ 34-40 )

3. መፅሃፍ ቅዱስዎን እንዲያጠኑ !
   በሕይወትዎ የሚያጋጥምዎን ጥያቄዎች መመለስ የሚችል እርሱ ብቻ ነዉና ።
   " ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነዉ ። ( መዝ ( 119 ) ÷ 105 )

4. ያገኙትን ሕይወት ሌሎችም እንዲያገኙ ይናገሩ ፣ የሆነለዎትን ያካፍሉ !

" የእዉነትን ቃል በቅንነት የሚናገር ፣ የማያሳፍርም ሰራተኛ ሆነህ
የተፈተነዉን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ ። " ( 2ጢሞ 2 ፥ 15 )

ራስዎንም በፀሎት መደገፍ አይዘንጉ ።

እግዚአብሔርም የየዕለቱን ጉጉትዎን ያድርግልዎ ።

( በማንኛዉም ጊዜ በስልካችን ወይም በኢ-ሜል አድራሻችን ሊያገኙን ይችላሉና
ይህንን እንዲያደርጉ እናበረታታለን ። )

የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ሕብረት
ቤተ-ክርስቲያን በሎስ አንጀለስ

ስልክ ፦ (323) 731-8721 ***ext. 102 , 103***

teket@ethiochristian.org